በሙከራ ውስጥ ያለፉት ቤተ ክርስቲያን

The Resource Center
SIM International
P.O. Box 7900
Charlotte, NC 28241

የሽፋን ፎቶ ፤ አባባ ደባቄ ጉንፋሮ ከሲዳማ
ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
ቀዳሚ አማኞች አንዱ ።
(ፎቶ ፤ ወ·ዓ 1988)

II

በመከራ ውስጥ ያበበች

ቤተ ክርስቲያን

ከ

ወንድዬ ዓለ

ቅጽ አንድ

(ከ1920 - 1933)

ኤዲተር

ጌታቸው በለጠ

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን

ታሪክ

ሰኔ 1990 ዓ.ም

በመከራ ውስጥ ያበበች ቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ቅጽ አንድ (1920 -1933)

Copyright©1998 - KHC Literature Department

Church out of Tribulation (The Story of The Kale Heywet Church in Ethiopia)

(Vol. One 1928-1941)

All rights reserved. No portion of this book may be reproduced in any form what so ever, except for brief quotations in reviews, with out the written permission of the publisher.

አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር በምንም ዓይነት ሁኔታ ቢሆን ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛት፥ በኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች መቅረጽና ማራባት በፍጹም የተከለከለ ነው። ለጥናታዊ ጽሁፎች ማጎልበቻነት ከሆነ ግን ውሱን ሃሣቦችን ከመጽሐፉ ውስጥ መጥቀስ የተጠቃሚዎች መብት ነው።

አሳታሚ፤ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሥነ ጽሑፍ አገልግሎት

Publisher ; The Ethiopian Kale Heywet Church Literature Department

የኮምፒውተር ሥራ፤ ውቢት ኑራም

Tel. 51 58 44
ስልክ. 15 41 70
51 96 44

Fax. 251-1-51 27 63
E-Mail AMKHC @ telecom-net.et
ፖ.ሣ.ቁ P.O. Box 5829

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
Addis Ababa - Ethiopia

ምስጋና

በዚህ የታሪክ መጽሐፍ ዝግጅት ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ በማድረግ የተባበሩንን፥

- የአማካሪ ቡድን አባላትን
- ገምጋሚዎችን
- የታሪክ መረጃዎችን በመስጠት የተባበሩንን
- የገንዘብ፥ የማቴሪያልና የሞራል ድጋፍ ያደረጉልንን፥
- የኤስ.አይ.ኤም ኢንተርናሽናል ቢሮና የኤስ.አይ.ኤም ኢትዮጵያ ቢሮ የሥራ ኃላፊዎችን፥

እና የሥራችን ተካፋይ በመሆን በዚህ ታላቅ አገልግሎት ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከጎናችን ሳይለዩ በተለያዩ አቅጣጫዎች ለረዱንና በፀሎት ለደገፉን ሁሉ ልባዊ ምሥጋናችንን እናቀርባለን።

"እግዚአብሔር ቅን ፈራጅ ስለሆነ. . . ቅዱሳንን በመርዳት ስለለመዱ ያሳያችሁትን ፍቅር አይረሳም።" (ዕብ. 6 :10)

በዚህ የታሪክ መጽሐፍ ሥራ ላይ ተሣትፎ ያደረጉ

I. የአማካሪ ቡድን አባላት

1. አቶ ተክሌ መ/ጊዮርጊስ
2. አቶ ማሞ ገ/መስቀል
3. ዶ/ር ፒተር ኮትሬል

II. ረቂቁን በመገምገም የረዱን

1. ዶ/ር ሙላቱ ባፋ
2. አቶ ሽፈራው መ/ሚካኤል
3. ዶ/ር ተስፋዩ ያዕቆብ
4. አቶ ደምሴ ማዴ
5. አቶ አይዲቆ አየለ
6. አቶ ጥላሁን ኃይሌ
7. አቶ ማሞ ገ/መስቀል
8. አቶ ኩርሴ ሽፈኖ
9. ዶ/ር ፒተር ኮትሬል
10. አቶ ብርሃኑ ደረሰ
11. አቶ ዘለዓለም መንግሥቱ
12. ዶ/ር ፖል ብልስኪ
13. አቶ ደስታ ደምሴ
14. አቶ ከልክላቸው ዓሊ. . . ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አንትሮፖሎጂስት

ማውጫ

ገጽ

ጥቂት ቃል XI
አስተያየት XIII
መቅድም XV
መግቢያ XVII

ምዕራፍ አንድ
የወንጌል ዘር በኢትዮጵያ

1· ቅድመ ክርስትና 3
2· በኢትዮጵያ የክርስትና አጀማመር 5
3· የጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን መስፋፋት 11
4· የወንጌል ይዘት በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን 13
5· ስብከተ ወንጌል ኦርቶዶክሳዊ ተሞክሮ 18
6· ተቀጣጥሎ የከሰመ ወንጌላዊ መነቃቃት 27

ምዕራፍ ሁለት
የሚስዮናውያን ታሪክ በኢትዮጵያ

7· የሚስዮናዊነት ፅንሰ ሀሳብ 33
8· የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናዊያንና አመጣጣቸው 34
9· የፖርቹጋል ሚስዮናውያን 36
10· የኢየሱሳውያን መግባት 37
11· የመጀመሪያዎቹ ፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን
ሙከራዎች 39

ምዕራፍ ሦስት
የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት

12· በሩ ተንኳኳ 54

13· በሩ ተከፈተ 57

14· አጣማጅ ፍለጋ 61

15· አዋጅ ነጋሪዎች 66

16· ሊነጋ ሲል 77

17· ዘሩ በቀለ 97

18· ድንበሩ ሰፋ 100

19· የመስፋፋት ሙከራ በሰሜን ኢትዮጵያ 107

ምዕራፍ አራት
የመጀመሪያው መከር

20· ከመከር በፊት 115

21· የመጀመሪያዎቹ ተጠማቂዎች 119

22· የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም 128

ምዕራፍ አምስት
ቤተ ክርስቲያን በጣሊያን ወረራ ዘመን

23· አጠቃላይ እይታ 135
24· የሚስዮናውያን መባረር 137
25· የአገልግሎት ርክክብ 141
26· የኢጣሊያ የሃይማኖት ፖሊሲ 144
27· በጊዜውም ያለጊዜውም 150

ምዕራፍ ስድስት
የፈተናው ሰንሰለት

28· ሦስት ቀለበቶች 161
29· የመከራው ገፈት ቀማሾች 167

ምዕራፍ ሰባት
የመከራው ማዕድ ተቋዳሾች

30· ቶሮ ፤ ጋፈቶ ፤ ዳና ገደቦ 195
31· ብሩ ከሞት ወዲህ ማዶ 208
32· ዳና መጃ መዳሮ 217
33· አቶ ሽጉጤ ዳዳ 224
34· አባ ጎሌ ኑነሞ 233

ጥቂት ቃል . . .

እግዚአብሔር እስከአሁን በሰጠኝ ዕድሜ ብዙ ነገሮችን ከእግዚአብሔር ለማግኘትና ለመጨበጥ ተመኝቻለሁ። ብዙዎቹ ምኞቶቼን እግዚአብሔር በራሱ ጊዜና መንገድ ሣራ ይስሐቅን እንዳቀፈች አሳቅፎኛል። የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ መፃፍ ለእኔና ለሌሎችም የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች የረጅም ጊዜ የልባቸው አምሮት ፍፃሜ እንደሆነ አስባለሁ። ስለዚህም ለታላቁ አምላካችን ከልባችን የመነጨ አክብሮት የተሞላበት ምሥጋናችንን አቀርባልሁ።

ስለ ኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሲጻፍ ይህ የመጀመሪያው መጽሐፍ አይደለም። መጠነኛ ቁጥር ያላቸው የውጭ አገር ሰዎች የተለያዩ መጻሕፍትን ጽፈዋል። በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ሲጻፍ ግን ይህ ሙከራ የመጀመሪያውን ከፍተኛ ደረጃ ከመያዙም በላይ በቤተ ክርስቲያኒቱ አጠቃላይ ገጽታ የነበረውን ጉልህ የሆነ ባዶነትም እንደሚሞላ ይታመናል። ይህ ብቻም ሳይሆን በብዙ መልኩና ገጽታው በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት ውስጥ የነበረውንም ክፍተት ሊያቀራርብ እንደሚችል እናምናለን። በተለይም ከኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ወጥተው በሌሎች ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ "ዋነኞች" የሆኑትን ወገኖች ቁጥር ስናይ ይህ አነጋገር የበለጠ እውነተኛነት ይኖረዋል። የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የአገራቱን ሰፊ የቆዳ ክልል ከመሸፈንና በምዕመናን ቁጥር ብዛት ከሌሎቹ የአገራችን ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎላ ያለ በመሆኑም ጭምር ይህ አነጋገር እውነትነት አለው እላለሁ።

ይህ መጽሐፍ በዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ የቻለው ረጅም ታሪክ አልፎ ነው። ብዙ ወገኖች የቤተ ክርስቲያናቸው ታሪክ እንዲጻፍ መመኘታቸው እውነት ነው። የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክ ለመጻፍ የመጀመሪያው ሙከራ የተደረገው ምናልባትም በኔ ሳይሆን አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። በሰኔ ወር 1966 ዓ.ም. በቃለ ሕይወትና በኤስ. አይ. ኤም. መሪዎች መካከል በቢንጋሃም አካዳሚ በተደረገው ስብሰባ ላይ የቤተ ክርስቲያኒቱን ታሪክ ለማሰባሰብና ለመጻፍ ይቻል ዘንድ ባለ ሁለት ገጽ መጠይቅ በተንሁ። ይህ ጥረት ከዚህ ደረጃ አላለፈም። ቀጥሎም በ1978 ዓ.ም. በቦርድ ውሳኔ

መሠረት ከዚህ የተሻለ ጥረት ተደርጎ የተወሰነ መረጃ ተሰባስቦ መጠነኛ ገፆች ያለው ያልታተመ ጥራዝ ለንባብ በቅቷል።

ይህ መጽሐፍ ግን በምርምር ጥልቀቱ በጣም የተሻለ ነው። ተመሳሳይ ጥረት ቀደም ብሎ ባለመደረጉም የተነሳ መጽሐፉን ለማዘጋጀት ልባቸው በውስጣቸው የተቃጠለው ወገኖች በተለይ ወንድዬ አሊ በሕይወት ካሉት አባቶችና እናቶች ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት የዘመናት መፈራረቅ በፈታቸውና በግንባራቸው ላይ የሠራውን ሽንተረር እያስተዋለና ዘመን ያዳከመውን የሰለለ ድምፅ እያደመጠ ታሪካቸውንና ወጋቸውን ሊቀርጽ በቅቷል። መኪና በተሸነፈበት በፈረስ፥ ፈረስ በተቸገረበት በእግር ብዙ ተራሮችንና ቁልቁለቶችን ወጥቶ ወርዷል። አርኪዮሎጂስቶች ቅሪቶችን ለማግኘት በቅሪቶቹ ላይ የተከመሩትን ብዙ ነገሮች በቁፋሮ እንደሚያነሱ ሁሉ ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት የ70 ዓመታት ዘመንና ሕይወት ሲያልፉና ሲያገድሙ የጫኑትን ክምር እያንገዋለለ መበርበር ነበረበት። ይህ ጥረቱና ልምዱ እራሱን ከታሪክ ፀሐፊነት ወደ ታሪክ መሆን የለወጠው ይመስለኛል።

እግዚአብሔር ሰውን ከሚባርክበት መንገድ አንዱ ለሰው ሰውን በመስጠት ነው። ወንድዬ በተለይ ለዚህ ታላቅ ሥራ ለኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እንደተሰጠ ሁሉ እንዲሁም ወንድማችን ጌታቸው በለጠ ለወንድማችን ወንድዬ ተሰጠ። ቃላትን በመደፍጠጥ፥ በማርዘም፥ በማሳጠር፥ በማወረርም ሆነ በማቅጠን እንደልቡ የመጫወት ስጦታ የተጎናፀፈው ወንድማችን ጌታቸው በለጠ ለመጽሐፉ ውበትና ተነባቢነት ግሩም የሆነ አስተዋጽኦ አድርጓል። ጌታ እነኚህን የኛ ምትኮችን ስለሰጠን እጅግ እባርከዋለሁ። ለእነርሱም የማያልቅበት እግዚአብሔር ሁለንተናዊ በረከቱን ያብዛላቸው።

ይህን የታሪክ መጽሐፍ የማናቸውም ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችና መሪዎች ሊጠቀሙበት ይገባል ብዬ አምናለሁ።

"የተፈጸመች ፈቃድ ሰውነትን ደስ ታሰኛለች "(ምሳሌ 13:19) ተብሎ እንደተፃፈ የኔ ልብ ደስ ብሎታል። የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ልብ ደስ እንደተሰኘ አምናለሁ።መከናወንን ላደረገልን አምላካችን ክብር፥ ምሥጋናና በረከት በእጅጉ ይሁን። አሜን!

ሽፈራው ወ/ሚካኤል
የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት
ቤተ ክርስቲያን ሊቀመንበር

ይህ መጽሐፍ የታሪክ ዳኛና ባለቤት የሆነው ሕያውና ዘላለማዊ አምላክ እግዚአብሔር በአገራችን የተለያዩ ክፍሎች ለቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መወለድና ዕድገት የተለያዩ ባሪያዎቹን ተጠቅሞ የሰራውን ድንቅ ተዓምራት የዘገበ ምስክር ነው።

ታሪኩ የሚገልጸው የሰውን ሳይሆን የመለኮታዊውን አምላክ ሥራ ነው። አምላካችን በቅዱስ አሰራሩና መንፈሱ ባሪያዎቹን አባቶቻችንንና እናቶቻችንን ስለተጠቀመባቸው ስሙ ይክበር። የታሪኩን ሁለንተናዊ ገጽታ የሚያውቀው እርሱ ባለቤቱ ሕያው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሆኖም ባለፉት ዘመናትና ዛሬም ላሉት ወገኖቻችን የተገለጸውንና የታወቀውን ገጽታ በዚህ ጽሑፍ ለማቅረብ የተቻለውን ያህል ጥረት ተደርጓል።

ይህ የአምላካችን ሥራ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ይታወቅ ዘንድ ይገባል። ስለዚህም ተጽፏል። ከመጽሐፉ ዝግጅቶች አንዱ የአባቶችንና የእናቶችን ታሪክ ወደየአካባቢው በመሄድ መሰብሰብ ነበር። በዚህ በኩል የሥነ ጽሑፉ ክፍል ባለሙያዎች ብርቱና ትዕግስት የተሞላበት ጥረት አድርገዋል። ሆኖም መጽሐፉ በዓይነቱ የመጀመሪያ ስለሆነ ያልተደረሰባቸውና ያልተዳሰሱ ታሪኮች ገና ሊኖሩ ይችላሉ። ከሆነም የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮችና ምዕመናንም ሆኑ ሌሎች አንባቢያን ይህንኑ ይገልጹልን ዘንድ በትህትና እንጠይቃለን። ቀሪዎቹ ዝርዝር ታሪኮች በሁለተኛው መጽሐፍ በቅርብ ጊዜ እንደሚታተሙ ለመግለፅ እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሰባኛ ዓመቷን ልታከብር በተቃረበችበት በዚህ ታሪካዊ ወቅት ይህ ጽሑፍ ለእግዚአብሔር ክብር፥ ላለፈው ትውልድ መታሰቢያ፥ ለአሁኑና ለሚቀጥለው ትውልድ የመንፈስ ቅዱስን ድንቅ አሰራር የሚያበስር ይሆን ዘንድ ጸሎቴና ምኞቴም ነው።

ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሁን

ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ

መቅድም

የዚህ መጽሐፍ ይዘት የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደተወለደች፥ እንዳደገችና ምእመናኗም ስላለፉበት ያልተቋረጠ የፈተና ሰንሰለት የሚያትት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ አንባቢው ቤተ ክርስቲያን በቅላ ያበበችበትንና ያፈራችበትንም ዘመን ዙሪያ ገቡን እንዲዳስስ በተቻለ መጠን አገናዛቢ መረጃዎችና ሐተታዎች እንዲኖረው ጥረት ተደርጎበታል። ጥረቱንም ለማሳካት የየጊዜው መንግሥታዊ ሥርዓቶች፥ የመሬት ይዞታ ስሪቶች፥ ማኅበራዊ ግንኙነቶችና የአምልኮ መገለጫዎች በመጠኑም ቢሆን ተነካክተዋል።

በተጨማሪም የአብዛኛው ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን ስለአጠቃላዩ የኢትዮጵያ ክርስትና ታሪክ ያላቸውን ግንዛቤ ለማስፋት ሲባል ከሺህ አምስት መቶ ዓመታት በላይ ወደኋላ ሄደን ስለመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረትና እድገት እንዲሁም የተካሄደውን አገልግሎት የወንጌል ይዘት ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል። መነሻችንን በሚገባ ስናውቅ በብሔራዊና በአገርኛ ጉዳዮቻችን ላይ በራስ የመተማመንና የራስን የማክበር ስሜት ለመገንባት ያስችለናል።

ሥራው ገና ሲታቀድ በተመረጠለት ስልት መሠረት ተነባቢ እንዲሆንና ሕይወት ሕይወት እንዲሸት ብዙ ተደክሞበታል። መፍትሔ ያልነው ስልት የቤተ ክርስቲያንን የረጂም ዘመናት ታሪክ ከቀደምት አባቶች የሕይወት ምሥክርነት ጋር በመሸረብ ማቅረብን ነው።

መልካም ንባብ።

የድሮውን ዘመን አስብ፥
የብዙ ትውልድንም ዓመታት አስተውል፤
አባትህን ጠይቅ፥ ያስታውቅህማል፤
ሽማግሌዎችህን ጠይቅ፥ ይነግሩህማል።
(ዘዳግም 32፡7-8)

መግቢያ

እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራው የሰው ልጆችን በመጠቀም ነው። ከትውልድ መካከል የፈለገውን ሰው ለይቶ ዓላማውን ይፈጽምበታል፤ ያስፈጽምበታልም። ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ ሰጥቶ ሜንቃውን "ለቀምበሩ " ልቡን ለፈቃዱ ያስገዛ ትውልድ ደግሞ ዘሩ ይባረካል፤ ቀጣዩ ትውልድም ይለመልማል ። አልፎም ተርፎ የረገጠው ምድሩና ርስቱ የበረከት ፍሬ ጎተራ ይሆናል።

በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የታሪክ ማኅደር ውስጥም እነዚህ እውነታዎች በምሉዕነት ተንፀባርቀዋል። የሰባ ዓመት ታሪክ፥ በመዝሙር ዳዊት መጽሐፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው፥ የአንድ ሰው የዕድሜ በረከት ነው። ልዩነቱ የአንድን ሰው የሕይወት ታሪክ የመዘገብ ያህል የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ መተረክ ያለመቻሉ ነው። በተለይም በዘርፈ ብዙ የመከራ እሳት እቶን ውስጥ ነጥሮ የወጣን ታሪክ በዕለት ተዕለት የመግባቢያ ቋንቋ አጉልቶ ለማሣየት መሞከር ለታሪክ ዘጋቢ ባለ አደራዎች ምን ያህል ሊከብድ እንደሚችል መገመት አያዳግትም። ያዳግት ይከበድ እንጂ "ሀ" ተብሎ መጀመር እንዳለበት ግን ሁሉም የሚገነዘበው እውነት ነው። የእምነታችንና የእውነታችን መልሕቅ ይህ ስለነበር ይህንን የታሪክ መጽሐፍ "ቅጽ አንድ" በዚህ እውነታ መነሻነት ለንባብ ለማብቃት ተሞክሯል።

በአገራችን የታሪክ አመዘጋገብ ሂደት ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የመረጃ ማነስና የታሪክ መረጃዎች እጦት ትልቁ ችግር ቢሆንም በአገርኛና በውጭ አገር የታሪክ ምሁራን የተፃፉትን ምንጮች ንባባት በሕይወት ከሚገኙ እማኝ ምሥክሮች አንደበት ጋር በማዋሃድ ችግሩን ለማቃለል ተችሏል።

የመጀመሪያ መነሻችን በሕይወት ያሉትን ህያው ምሥክሮች ማድመጥ ነበር። በብዙ ትግልና ውጣ ውረድ ተወጣነው። የታሪክ መረጃዎችን የማፈላለጉና የበርካታ መጻሕፍት ንባባትም በዓመታት የሚቆጠሩ ጊዜያት ወስዶብናል። በዚህን አካሄድ ከተሰበሰቡት እጅግ በርካታ መረጃዎች ውስጥ የፍሬውን ምርት ለይቶ ለአንባቢያን ማቅረቡ ትልቁ ወሳኝ ፈተና ነበር። ይሄው በእግዚአብሔር ቸርነት ከክምር የታሪክ አውድማ ላይ ተመርቶ የወጣው ፍሬ ለጎተመት ብርሃን በቅቶ ለአንባቢያን ቀርቧል።

የአትኩሮት አቅጣጫቸውን ወደ ምዕራቡ የአገሪቱ ክፍል አድርገው ከሩቅ አገር ስለ ወንጌል ፍቅር የመጡት ሚስዮናውያን በእግዚአብሔር ምሪት መንገዳቸውን ስተው ራሳቸውን ደቡብ ኢትዮጵያ በማግኘት የወንጌልን ዘር በእምነት ዘሩ።

ያ ቅንጣት ዘር ዛሬ የብዙዎች መጠለያ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን አብቅሎ አፈራ። በተወሰነ አካባቢ የፈነጠቀው ብርሃን በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች ተቀጣጥሎ እነሆ ነፀብራቁ የጨለማ ሥራዎችን በመግለጥ የወንጌሉ የምሥራች ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ መጥቶ ዛሬም የአምላካችን ገናናነት በመላው አገሪቱ ለመታወጅ በቅቷል።

ይህ ቅጽ አንድ መጽሐፍ በዋነኛነት ያተኮረው ከ1920-1933 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት ውስጥ በተፈፀሙት ዋና ዋና ታሪኮችና ባለ ታሪኮች ላይ ቀዳሚ አፅንዖት በመስጠት ነው። የእግዚአብሔር አምላካችን መልካም ፈቃድ ቢሆን ቅጽ ሁለትም በዚሁ አካሄድ ይቀጥላል።

ለዚህ መጽሐፍ ሥራ በዋነኛነት ምርኩዝ የሆነን መሪ ጥቅስ፤


" የዱሮውን ዘመን አስብ
የብዙ ትውልድንም ዓመታት አስተውል፤
አባትህን ጠይቅ፥ ያስታውቅህማል፤
ሽማግሌዎችህንም ጠይቅ፥ ይነግሩህማል።" (ዘዳ. 32:7-8)

የሚለው ነው። እነሆ አባቶቻችን የነገሩን፥ ታሪክም ያረጋገጠው የወንጌል ውጣ ውረድ።

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሥነ-ፅሁፍ አገልግሎት
አዲስ አበባ ፥ ኢትዮጵያ

ምዕራፍ አንድ

የወንጌል ዘር በኢትዮጵያ



ዓይነተኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመስቀል ቅርጽ

ምንጭ ፡ The Ethiopian Orthodox Church 1970.

1. ቅድመ ክርስትና

የቅድመ ክርስትና ኢትዮጵያ መልክ ምን ይመስል እንደነበር አጠቃላይ ቅኝት ማድረጉ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ስለነበረው ሁኔታ ግንዛቤ ሊሰጠን ስለሚችል በዚሁ መነሻነት እንንደረደራለን።

የሰውን ልጅ ጥንተ አመጣጥና ስርጭት ዕውቀት ከዘመናዊው አንትሮፖሎጂ (የሥነ ሰው ጥናት) ይልቅ ዋና ምንጫችን ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነታ እንደምንገነዘበው (ዘፍ. 10 :22-29) በቅድሚያ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ነገዶች የካም ዝርያ የሆኑት ኩሻውያን ናቸው። እነዚህ የነገደ ኩሽ ዝርያዎች ምስርን (የአሁኗን ግብጽና የአካባቢውን ተጎራባች አገሮች ጭምር በማካለል) ወደ ደቡብ ባለው አገር ይኖሩ ነበር። በተመሣሣይ ጊዜም ከሴም ነገድ ውስጥ የተወሰኑቱ አሁን ደቡብ ዓረብ በምንለው አገር ይኖሩ ነበር። ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላም ከፊል ነገደ ሳባውያን ወደ አሁኑ ሰሜን ኢትዮጵያ ወይና ደጋማና ደጋማ አካባቢዎች ጥቂት በጥቂት እየመጡ መስፈር ጀመሩ።አንዳንድ ምንጮች እንደሚዘግቡት ይህ ሠፈራ በሚከናወንበት ጊዜ የኩሽ ሕዝብ ቀድሞውኑ የተደራጀ ነበርና በንግድና በዘላንነት እየመጡ የተቀመጡትን እኒህን ሰዎች ወግቶ ሊያባርር ሞክሯል። የአዲሱ መጤ የሳባ ነገድ አባላትም በጊዜ ብዛት ኃይላቸው እየተጠናከረ በመሄዱ አሸነፉና አካባቢያቸውን በቁጥጥራቸው ስር አደረጉ። ራሳቸውንም አግዐዝያን " ነፃ ወጭዎች " ብለው መንግሥት መስርተው መኖር ጀመሩ። የአክሱምን መንግሥት ለመመስረት የበቃውና ቋንቋውም ሳባውያን በመባል በታሪክ የሚጠቀሰው ይህ ሕዝብ ነው። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ አንድ የታሪክ ምሁር እንደሚከተለው ዘግበዋል፤

> . . .የሳባ ነገድ በየመን ግለትም በአሁኑ ደቡብ አረቢያ አይሎ መንግሥትንም አቋቁሞ ሲኖር ከብዙ ጊዜ በኋላ የኩሽ መንግሥት ካገር ሊያሳድዳቸው ጦርነት ቢያነሳባቸው ወይም ሌሎች ባለታሪኮች እንደሚሉ ራማ የሚባል የህንድ ንጉሥ መጥቶ የኩሽን መንግሥት በወረረ ጊዜ ሳባውያኑ በጦርነቱ ከእርሱ በርትተው በእነርሱ አነጋገር የዘንዶ መንግሥት የሚሉትን መንግሥት በኃይል አፈራረሱ። የአገሪቱንም ሥልጣን ራሳቸው

ያዙና አግዐዝያን (ነፃ ሕዝብ) ተብለው የራሳቸውን መንግሥት አቋቋሙ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያውያንን መንግሥት በአከሱም የመሰረቱ እነዚህ ሳባውያን መሆናቸው ነው። ለዚሁ መረጃ የሚሆን በትግሬ አውራጃዎች ሳባ፥ አንሳባ የሚባሉ ቦታዎች አሁንም ይገኛሉ።[1]

መጽሐፍ ቅዱስ በመረጃነት እየተጠቀሰ የሚዘከረው ሌላው ታሪክ የነገደ እስራኤል ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ነው። የዚህን ታሪክ መነሻ ምንጭ የምናገኘው ከታሪክ ነገሥት ነው። የሳባ ንግሥት ተብላ የተጠቀሰችው ንግሥት ወደ ኢየሩሣሌም በመሔድ ዝናው ገንኖ የወጣውን ንጉሥ ሰለሞንን በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች ፥ የሚለውን እናነባለን። 1ነገ. 10:1-13። ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታ በመነሻነት በመጠቀግ ሌላ አፈ ታሪክም በተጓዳኝነት ይጠቀሣል።ንግሥቲ ሳባ ንጉሥ ሰለሞንን ጎብኝታ ስትመለስ አርግዛ ነበርና ከተመለሰች በኋላ ቀዳማዊ ምኒልክን ወለደች። ምኒልክ ለአካለ መጠን እንደደረሰ አባቱን ለመጎብኘት ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ለሦስት ዓመታት ያህል ቆይቶ ሲመለስ ከእርሱ ጋር በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ከእስራኤል ነገድ ተከትለውት መጡ ይላል።[2]

ከታሪኩ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ብዙ አፈ ታሪኮች ቢኖሩበትም በኋለኛው ዘመን ፈላሻ ተብሎ ለሚታወቀው ክፍለ ሕዝብ መገኘት እንደ ዋነኛ ምንጭ ሆኖ የሚጠቀስ ታሪክ ነው። በብሉይ ኪዳን "የሳባ ንግሥት" የተባለችው በአዲስ ኪዳን "ንግሥተ ዓዜብ" ተብላ በጌታ በኢየሱስ የተጠቀሰችው ናት ማቴ. 12፡42። " ዓዜብ " በደቡብና በምዕራብ መካከል ያለ ንውስ አቅጣጫ ሲሆን አዲስ ኪዳን የተፃፈበት የግሪክ ቋንቋ ግን ደቡብ በማለት ብቻ ነው የሚጠቅሰው። ኢትዮጵያም ሆነች ዐረቢያ ከእስራኤል በስተ ደቡብ ስለሚገኙ ስለዚህ ዓዜብ ስለሚባለው ምድር ከአዲስ ኪዳንም ጥርት ያለ መረጃ አናገኝም።

ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር መጥተዋል ከሚባሉት ሌላ ተጨማሪ አይሁዶች ወይም እስራኤላውያን ከምርኮው በኋላ እና ኢየሩሳሌም በሮማዊው በጥሪስ ወረራ በ 70 ዓ.ም በወደቀችበትና በተበታተኑበት ወቅትም [3] በደቡብ የመን አድርገው መጥተው ሊሆን ይችላል። ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች ሳቢያ በኢትዮጵያ ውስጥ የብሉይ ኪዳን እምነት

ወይም የአይሁድ ሃይማኖት ተከታይ ቤተ እስራኤላውያን መኖራቸው እውቅ ነው። ይሁን እንጂ የአይሁድ እምነት የመንግሥት እና የአገር ሃይማኖት ሆኖ ስለመቆየቱ የሚቀርብ ተጨባጭ ማስረጃ የለም። ከክርስትና በፊት የነበሩት የጥንታዊ ነገሥታት የገንዘብና የሐውልት ምልክቶች ሁሉ የነበራቸው ቅርጽ የነገሥታቱን ጣዖት አምላኪነትን የሚያመለክት እንጂ የአይሁድ እምነት ተከታይነታቸውን ምንም ፍንጭ የሚሰጥ መረጃ አልተገኘም። ነገር ግን ከፊል ጣዖታዊ አምልኮ ከፊል ደግሞ አይሁዳዊ ሃይማኖት ከክርስትና በፊት እንደነበር አንዳንድ የታሪክ ምሑራን ጽፈዋል።

2. በኢትዮጵያ የክርስትና አጀማመር

ከአዲስ ኪዳን እንደምናገኘው መረጃ ከሆነ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ፊልጶስ በጋዛ መንገድ አግኝቶ ክርስቶስን የሰበከለትና ያጠመቀው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ነበር። (የሐዋ. 8:26-38)። ይህ ጃንደረባ የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ህንደኬ አዛዥ ነበር ። ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ሊሰግድ በመሆኑ የአይሁድ እምነት ተከታይ ሳይሆን እንደግይቀር ይገመታል። ይህ ባለስልጣን እንደ አይሁድ እምነት ተከታይ ሄዶ ክርስቲያን ሆኖ መምጣቱን እንጂ መጥቶ ምን እንደሠራ በተለይም የክርስትናን እምነት በመትከልና በማስፋፋት ረገድ ያደረገው ነገር ስለመኖሩ በተጨባጭ የጽሑፍ ማስረጃ ማረጋገጡ ያዳግታል ። አንዳንድ ትውፊታዊና አፈ ታሪካዊ ምንጮችን መነሻ የሚያደርጉ ጽሑፎች እንደሚዘግቡት ከሆነ ግን ይህ ሰው የክርስትናን እምነት በ34 ዓ.ም ገደማ ወደ አገራችን ይዞ የገባው ቀዳሚ ሰው ሲሆን ወንጌልን መስበኩና ቤተ ክርስቲያንን መመስረቱ ይነገራል።[4]

የዚህን ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ የወንጌል አገልግሎት በተመለከተ የሥነ መለኮት ሊቃውንት በየዘመናቱ የራሳቸውን አስተያየት መስጠታቸው አልቀረም። አንዳንዶች "መጽሐፍ ቅዱስ የሰጠን መረጃ ብቻውን በቂ ነው። ፊሊጶስ ወንጌል ከሰበከለት በኋላ ምን ውጤት አስመዘገበ? የሚለው ጥያቄ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጥ ስላልሰፈረ የግል ሃሣብን መነሻ በማድረግ ለውይይት መቅረብ የለበትም " ይላሉ።

አንዳንድ ምሁራን ደግሞ ይህንን ሃሣብ በፍጹም አይቀበሉትም። ለአብነት ያህል አንድ የሥነ መለኮት ምሑር በአንድ ስብሰባ ላይ ይህንን ጉዳይ አስመለከተው የተናገሩትን ሃሣብ እንዳለ እንጠቅሰዋለን፤

> ለመሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ ማስረጃ ከየት ማግኘት ይቻላል? ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወንጌል ተቀብሎ ያውም ፊሊጶስን መንፈስ ቅዱስ አጣድፎት ሰውዬውን አግኝቶ ወንጌልን አስተምሮ አጥምቆታል። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተለወጠ ሰው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ዝም ብሎ ኖረ ለማለት እንደምን ይቻላል? ለቤተሰቡ ለጓደኞቹና ለሌሎችም የሰማውን የወንጌል ቃልና አለዋወጡን እየተደነቀና እየተገረመ ሳይመሰክር ይቀራል?! ...በርግጥ በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ወንጌልን ተቀብሏል ወይም በጃንደረባው ምክንያት ጅምላ የሕዝብ ለውጥ ተፈጽሟል ብሎ ለመናገር ያዳግታል። [5]

አስተያየቱ ተጨማሪ ጥናት እንዲደረግ የሚጋብዝ መሆኑን በማስገንዘብ በዚሁ እናልፈዋለን።


ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በመቀጠልም በተቀራረበ የታሪክ ዘመን ሐዋርያው ማቴዎስ የምሥራቹን ቃል ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱና ወንጌልን ሰብኮ ምዕመናንን በማፍራት ሰማዕት ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ " ነደባ " በሚባል ቦታ መሞቱን የሚናገረው በዐረብኛ የተጻፈ ስንክሳርና የቤተ ክርስቲያን ትውፊትም የሚጠቀስ ነው። [6]

ከላይ በጠቃቀሰናቸው ታሪኮች መሠረት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ገባ ከተባለበት ከ4ኛው ምዕተ ዓመት ቀደም ብሎም የወንጌል ዘር በኢትዮጵያ ተዘርቶ ነበር ለማለት ያስችላል። ነገር ግን ከክርስትና በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ እምነቱ ሙሉ ለሙሉ የእውነተኛው የእግዚአብሔር አምልኮ ብቻ ነው ማለት ግን ያዳግታል። አንድ ኢትዮጵያዊ የታሪክ ምሁር ይህን አስመልክተው ሲጽፉ፤

> እስከዛሬ ባገራችን ሊቃውንት ዘንድ የዚህ (የተለያዩ አማልክት መመለካቸው ማለት ነው) ልዩነት ሳይገለጽ ከክርስትና በፊት የኢትዮጵያ ነገሥታትና ሕዝብ ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ዠምሮ በውነተኛው እግዚአብሔር እያመለኩ እስከ ክርስትና ደረሱ የሚለው ትክክለኛና እውነተኛውን ታሪክ አልያዘም ብለን ለመጻፍ እንደፍራለን፤[7]

በማለት አቋም ወስደዋል። ከክርስትና በፊት የነበረው መልክ ይህን ከመሰለ በታሪክ ወደ ተመዘገበው የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ አገባብ እንመለስ።

የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአክሱም ዘመነ መንግስት በንጉሥ ኢዛና ዘመነ ንግሥና ወቅት ነው። (ይህ የአክሱማውያን መንግሥት ከ100 ዓ.ዓ . እስከ 975 ዓ.ም በፖለቲካ፥ በባህልና በንግድ ገናና ከነበሩት የፋርስ፥ የሮም፥ የቻይና መንግስታት አንዱ እንደነበር የአገር ውስጥና የውጭ አገር ታሪክ ጸሐፊዎች ይጠቅሳሉ።) ይህ ኢዛና በኋላ ክርስትናን ተቀብሎ አብርሃ የተባለው ነው።



የንጉሥ ኢዛና የወርቅ ገንዘብ
ክርስትናን ከመቀበሉ በፊት



የንጉሥ ኢዛና የወርቅ ገንዘብ
ክርስቲያን ከሆነ በኋላ

አንዳንድ የታሪክ ተመራማሪዎች ስመ ጥር የሆነውንና በአራተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የነገሠውን ንጉሥ ኢዛናን "የሐበሻ ቆስጠንጢኖስ" በማለት ይጠሩታል። በአክሱም ከነገሡት ሁሉ ይበልጥ ገናና ስለ መሆኑ ሥራውን የሚዘክሩት ድርሳናት ያረጋግጣሉ። ኢዛና አረማዊ ሳለ በሐውልት ላይ ያስጻፋቸው ጽሑፎችና በገንዘቡ ላይ ያስቀረጻቸው የግማሽ ጨረቃና የፀሐይ ምስሎችን ሲሆን፥ ክርስቲያን ከሆነ በኋላ ካስጻፋቸውና

ካስቀረጻቸው በይዘት ይለያሉ። ድህረ ክርስትና በወርቅ በተሠሩት ገንዘቦች ላይ የሚታየው የመስቀል ቅርጽ ሲሆን "የሰማይ ጌታ መንግሥቴን ጠንካራ ያድርግልኝ" የሚል ጽሑፍም ተቀርጾባቸዋል።

የዚህም ምክንያቱ ክርስትናን መቀበሉ ያመጣው ለውጥ ሲሆን በዘመኑም ክርስትና ወደ ቤተመንግሥት ገብቶ የነገሥታት ሃይማኖት መሆን የጀመረበት ዘመን ነው።

እንዴት ክርስትና በዘመነ ኢዛና ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ ቻለ? በሚለው ጥያቄ ላይ የተለያዩ ምንጮች የሚያወሱት ከዘመንና ከአንዳንድ አተራረክ በቀር ተቀራራቢ ታሪክ ስለሆነ ከታሪክ ነገሥት፥ ከስንክሳር ዘአባ ሰላማና፥ ከስንክሳር ዘገድለ ተክለ ሃይማኖት የተውጣጣውን አጠቃላይ ሃሣብ እንደሚከተለው በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል፤

መሮጵዮስ የተባለ በጢሮስ ይኖር የነበረ ነጋዴ ፍሬምናጦስና ሲድራኮስ የተባሉ ሁለት ወጣት ዘመዶቹን ይዞ ይሄዳል። አካሔዱ ለንግድ ይሁን ለሌላ ጉዳይ በግልጽ አይታወቅም ብቻ መርከቡ በቀይ ባህር ወደብ (ምጥዋ) ሲደርስ መሮጵዮስ በወንበዴዎች ይገደላል። ሁለቱ ወጣቶችም በምርኮ ተወስደው ለቤተ መንግሥቱ ይሰጣሉ። በጊዜው ንግሥት የነበረችው የነኢዛና እናት ባሏ ስለሞተ ልጆቿዋም ገና ለመንገሥ የደረሱ ስላልነበሩ የመንበረ መንግሥቱ ሞግዚት ነበረችና ወጣቶቹን ወስዳ ፍሬምናጦስን የልጆቿዋ አስተማሪ እንዲሆን አደረገችው። ሲድራኮስን ደግሞ የግምጃ ቤቷ ኃላፊ አደረገችው። ብዙ ዘመናት በሰላምና በመግባባት ከቆዩ በኋላ ወደ አገራቸው የመመለስ በጎ ፈቃድ አገኙ። ሲድራኮስ ወደ ሶርያ ሲመለስ ፍሬምናጦስ ክርስቲያን መሆኑ ብቻ ሳይሆን በቤተ መንግሥትም ውስጥ ክርስትናን በትንሹም ቢሆን አስተምሮ ስለነበር የአክሱምን መንግሥት የክርስትና ሁኔታ በቅርብ ሊረዳ ይችላል ብሎ ላመነው ለእስክንድርያ መንበር ለመንገር ወደ ግብጽ አለፈ።

በመልክአ ምድር ረገድም በጊዜው የቅርቧ ቤተ ክርስቲያን የግብጿ ነበረች። በዘመኑ የእስክንድርያ ጳጳስ ከነበሩት አትናቴዎስ ጋርም በሰፊው በመነጋገር ህዝቡ ክርስትናን ለመቀበል እንደሚፈልግ በማስገንዘብ ጳጳስ እንዲላክላቸው አሳሰበ። ጳጳሱም የአገሩን ቋንቋና ልማድ የሚያውቅ

ከፍሬምናጦስ የተሻለ ሰው አለመኖሩን በመግለጽ ራሱኑ የጵጵስና ማዕረግ ሰጥተውት ወደ ኢትዮጵያ መልሰው ላኩት። በ330 ዓ.ም ተመልሶ የመጣው ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሚቴ ብርሃን (የሰላም አባት÷የብርሃን ፈንጣቂ) በመባል አዲሱ እምነት ማስፋፋት ጀመረ።

የኢትዮጵያ ክርስትና ገና ከመጀመሪያው ከእስክንድርያ ክርስትና ጋር የተጣበቀውም በዚህ መልኩ ነበር። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ክፍለ ዘመናችን አጋማሽ ድረስ የኢትዮጵያ አርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ከእስክንድርያ ስታመጣ የኖረችው ከዚህ የጠበቀ ግንኙነት እና ኢትዮጵያውያን ከመካከላቸው ጳጳስ እንዳይሾሙ ከሚያግደው አከራካሪው የፍትሐ ነገሥት ትእዛዝ የተነሣ ነው። [8]

የአክሱምን መንግሥት በአደራ ከአስተዳደረችው ንግሥት አሕየዋ (ሶፊያ) በኋላም ሁለቱ ልጆችዋ ኢዛናና ሳኢዘናስ ስመ ክርስትናቸውን አብርሃ እና አጽብሃ አሰኝተው አብረው ነግሠው መግዛት ጀመሩ። ስማቸው አብርሃ(ብርሃን አመጣ)እና አጽብሃ(ንጋት አመጣ) የተባለውም ከክርስትና እምነት ወደ አክሱም መግባት ጋር ተያይዞ ነው። [9]

እንግዲህ የኢትዮጵያን ክርስትና በአጀማመሩና በመስፋፋቱም አንጻር በቀረቤታ ስንመረምረው ያስከተለው ለውጥ በተራው ሕዝብ ሕይወት ውስጥ ሳይሆን በቤተ መንግስት አካባቢ መሆኑን እንገነዘባለን፡ : ለዚህም ነው የክርስትና ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት ነበር የሚባለው።

እስክንድርያዊውንና መንግስታዊውን የኢትዮጵያ ክርስትና አቀባበል በተመለከተ ኡለንዶርፍ የተባሉ የኢትዮጵያ ታሪክ ምሁር እንደሚከተለው ገልጠውታል፤

> የአበሻ አገር (አቢሲኒያ) ወደ ክርስትና መለወጥ በጊዜ አንጻር ሲታይ ዝግተኛ÷ በመልክአ ምድር አንጻር ሲታይ ደግሞ ቢያንስ ከዋናዎቹ ማእከሎች ውጪ የሆነ ነበር። እንዲህ በመሆኑም በጣም ለተለያዩ የሃይማኖት ልግዶችና የልምምድ ደባል ሐረጎች አብረው ለመብቀልም ሆነ ለመደባለቅ ሁኔታዎች ተመቻችተውላቸው ነበር። ይህ በመጠኑም ቢሆን

በአበሻ ክርስትና ውስጥ የሚታየውን ጉልህ የሆነ ቅይጥነት ሊገልጥ ይችላል።[10]

እንደ ኡለንዶርፍ አገላለጥ ለዚህ ቅይጥነት አስተዋጽኦ ካደረጉት ጉዳዮች መካከል ፍሬምናጦስን ጨምሮ የመጀመሪያዎቹ ሶርያውያን ሰባኪዎች አሻራ እንዲሁም ከኬልቄዶኑ ጉባኤ በኋላ የተወገዙትና በጥገኝነት ለመኖር ከአገራቸው ተሰድደው በግብጽም በአረብም በአበሻም አገር የተበተኑት የአንድ ባህርይ (ተዋሕዶ) እምነት ተከታዮች ልምምዶች ናቸው።

ከነዚህም መካከል በ480 ዓ.ም ላይ ታዜና ወልደ አልዓሜዳ (የአልዓ ሜዳ ልጅ) የሚባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ ይገዛ በነበረበት ዘመንና በሁለተኛው የኢትዮጵያ ጳጳስ በአባ ሚናስ ጊዜ ወደ ሀገራችን የገቡትና ተሰዓቱ ቅዱሳን ወይንም "ዘጠኙ መነኮሳት" በመባል የሚታወቁት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከፍ ያለ ቦታ ተሠጥቷቸዋል። የእነዚህም መነኮሳት ዝርዝር ከመጡበት ሀገር ጋር እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፤[11]

	የመነኮሳቱ ስም	የመጡበት አገር	በስማቸው የተሰየሙ ገዳማት
1.	አባ አሌፍ	ቂሣርያ	ብጎዛን
2.	አባ አረጋዊ	ቁስጥንጥንያ	ደብረዳሙ
3.	አባ አፍጼ	ታናሹ እስያ	ዮሐ
4.	አባ ሊቃኖስ	ቁስጥንጥንያ	ደብረ ቆናጽል
5.	አባ ገሪማ	ቁስጥንጥንያ	መደራ
6.	አባ ጉባ	ኪልቅያ	ባርዳልታ
7.	አባ ይምዓት	ቆስያ	ገርዓልታ
8.	አባ ጳንጠሌዎን	ቁስጥንጥንያ	አክሱም (አጠገብ)
9.	አባ ጽሕማ	አንጾኪያ	ጼዴንያ

እነዚህ ዘጠኙ መነኮሳት የኬልቄዶንን ጉባኤና (451ዓ.ም.) ውሳኔውን አንቀበልም በማለታቸው በቢዛንታይን ነገሥታት ስቃይ ስለበዛባቸው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በሰሜን ክፍለ ሐገራት ተቀመጡ።

ዘጠኙ መነኮሳት ሥርዓተ ገዳምንና ምንኩስናን በከፍተኛ ደረጃ አስፋፍተዋል። የግዕዝን ቋንቋ ተምረውና አውቀው ከኢትዮጵያዊያን ሊቃውንት ጋር ሆነው አያሌ መጻሕፍትን ከዕብራይስጥ ከሱርስትና (አራማይክ)ከፅርዕ (ግሪክ) ተርጉመዋል። ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ጥንካሬ ከፍተኛ ተልዕኮን በመፈጸማቸው ቤተ ክርስቲያኒቱ ቅዱሳን ብላ ታከብራቸዋለች። ከላይ እንደተገለጸውም በስማቸው በርካታ ገዳማትን ሰይማላቸዋለች። ክርስትና በስፍራ ረገድ ሰፋ ያለ ዕድገት ያሳየውም ከነዚህ ሰዎች መምጣት በኋላ ነው።

3.የጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያንና መስፋፋት

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በኢዛና ዘመነ መንግስት ከሆነ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የተመሰረተችውም በዚያው በመናገሻ ከተማው በአክሱም መሆኑም የሚያጠራጥር አይደለም። እምነቱን ነገሥታቱና መኳንንቱ በመቀበላቸው ያለችግርና እንዲያውም በመንግሥታዊ ድጋፍና አሰሪነት የአብያተ ክርስቲያናት ሕንፃ ተገንብተዋል።

ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ስትቋቋም በአክሱም መጀመሪያ መስቀል በተተከለበት ቦታ በስፋት በርዝመትና በውበት ወደር የማይገኝለት...የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ተሠራ።ስለ አሰራሩ ሁኔታ አለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ ዝዋይ የተገኘውን ታሪክ ነገሥት በመጥቀስ እንዳብራሩት በ344 ዓ.ም. የተጀመረው ሕንጻ ሥራው የተጠናቀቀው ከ75 እስከ 91ዓመት በኋላ ነበር።[12]

እዚህ ላይ የሕንፃውን ታሪክ ለማውሳት ያህል እንጂ ቤተ ክርስቲያን ማለት በተለምዶ ብቻ ካልሆነ በቀር ሕንፃ ማለት ሳይሆን

የአማኞቹ ጉባዔ ማለት ነው ። በአራተኛ ምዕተ ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ የተመሰረተችው ይህች ቤተ ክርስቲያን ከዚህ በፊት ክርስቲያናዊ ግኅበር ቦግልጽ ባልታወቀባት ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሰረተች ጉባኤ እና ሕንፃ መሆኗ ነው።

> ፍሬምናጦስም ጵጵስናውን ተቀብሎ ከተመለሰ በኋላ በኢትዮጵያ የክርስትናን ሥርዓት አስፋፍቶ ሰበከ። የክህነትንና የቁርባንንም ሕግ አጠናከረ። በኢትዮጵያ ግዛት በሙሉ የወንጌልን ትምህርት ለማዳረስ የሚረዱ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ሾመ ::13

በመጀመሪያ ካመኑትና የክህነት ማዕረግ ከተቀበሉት መካከል ቀድሞም የነበረው የብሉይ ኪዳን እምነት ተከታዮችና መሪዎችም ነበሩበት። ከዚህም የተነሣ የብሉይና የአይሁድ ሥርዓትና ባህል የሆኑ አንዳንድ ልማዶች እንደማይወጡ ሆነው ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሠርገው ገቡ። ይህም ከካህናት አለባበስ ጀምሮ እስከ የቤተ መቅደስ ሕንፃ ቅርጽ፥ ግርዘትንና የመሳሰሉትንም ይጨምራል።

ስለዚህች የመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ስያሜና አደረጃጀት ሌላው ጸሐፊ እንዲህ ይላሉ፤

> እነሆም አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን በኢትዮጵያ ወንጌልን ሰብኮ ባስተማረ ጊዜ ወንጌልን በማመን የክርስትናን እምነት በተቀበሉ ምዕመናን አማካይነት የኢትዮጵያ የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ድርጅት አክሱም ላይ ተቋቋመ። የዚህ ቤተ ክርስቲያን መቋቋም ከአይሁድ፥ ከአሕዛብ፥ ካመኑና ከተጠመቁ ከተራ ሕዝብ፥ ከንጉሥና ከመኳንንቱም በጠቅላላው ወደ ክርስቶስ መንግሥት ከመጡት ከብዙ ወገን የተመሠረተ ጉባኤ ሆነ። እንግዲህ ይህ ጉባኤ ትልቅ ማኅበር መሆኑ ነው።
>
> ማንኛውም ማኅበር ሲቋቋም አንድ ብሔራዊ መጠሪያ ስም ሊኖረው አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን ይህም የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ "ማኅበረ ጽዮን ሰማያዊት " ተብሎ እንዲጠራ ተደረገ። ማኅበረ ጽዮን ሰማያዊት ማለት የሰማያዊት ጽዮን ማኅበር ማለት ነው።[14]

የዚህች ቤተ ክርስቲያን ሌላኛው ተቀራራቢ ስያሜ "የሐዲስ ኪዳን ጽዮን" የሚል ነው። ይህ ስያሜ ከታቦተ ጽዮንም ሆነ ከብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላነት ወይም የአሪት ባህል ጋር በቀላሉ ሊያያዝ የሚችል ነው። በታሪክ ነገሥት እንደተፃፈው ዝርዝር ከሆነ የሕንፃው አሰራር በጣም ትንግርታዊ ነው።የሕንፃውንም ሥራ በአጭሩ በዚሁ እንለፈው ምክንያቱም የሕንፃን ሥራ ከብሉይ ኪዳኑ ቤተ መቅደስ ጋር ካላያያዝነው በቀር በአዲስ ኪዳን ሕንፃና ቤተ መቅደስ የተባለው ራሱ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ነውና (1ቆሮ.3:9፥16፥6:19-20) የመጀመሪያዎቹ የአዲስ ኪዳን አማኞች በመቅደስ፥በምኩራቦች በቤታቸውም ሆነ በልዩ ልዩ ጸሎት ስፍራም ያመልኩ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።(ሐዋ 2:46፥16:16 ወዘተ)።

4. የወንጌል ይዘት በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ማለት ሕንፃው ሳይሆን ማኅበረ ምዕመናኑ ከሆነ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ማኅበርም በወንጌል ላይ የተመሠረተች በሐዋርያት እምነትና ትምህርትም የተደገፈች እንደሆነች ይታመናል። ምክንያቱም ከዚህ ጊዜ በኋላ የተከሰተው የካቶሊክና የኦርቶዶክስ መከፈል ገና አልታየም፥የግብጿም ቤተ ክርስቲያን በዚህ ጊዜ በሰሜን አፍሪቃ ከነበሩትና በመከራና በስደት እየታሹ ከወዙት አብያተ ክርስቲያናት አንዷ ነበረች። በታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤትም የተጀመረው በእስክንድርያ መሆኑና ቀሌምንጦስን እና ኦሪጀን (አርጌንስ)ን የመሰሉ አስተማሪዎች በዚህ ተቋም ውስጥ ማስተማራቸውና የእምነታቸው ዝክረ ታሪክ ዛሬም መኖሩ የጊዜውንና የአካባቢውን ጤናማ ክርስትና እንድናውቀው ያደርገናል።

የኢትዮጵያዋ ቤተ ክርስቲያን በተመሰረተችበት ዓመታት አካባቢ ማለትም ከመመስረቷ ጥቂት ዓመታት በፊትና በኋላ በሰሜን አፍሪቃ ቤተክርስቲያናት ዙሪያ የታዩ መሠረታዊ ችግሮች ነበሩ። ሥነ መለኮታዊ ስህተቶችም ታይተዋል። ይህ ወቅት በቤተ ክርስቲያን ላይ የመንግሥታዊ ተጽዕኖ ጥላ እያጠላ የመጣበትም ጊዜ ነበር። ለመንግሥታዊው ተጽዕኖ

መስፋፋት እንደ ዋና ምክንያት የሚጠቀሰው የቆስጠንጢኖስ ክርስቲያን መሆንና ክርስትና የብሔራዊ ሃይማኖት ቅርጽን መያዝ መጀመር ሲሆን ሥነ መለኮታዊውን ችግሮች በተመለከተም ተከታታይ ጉባዔዎች እየተሰየሙ ጉዳዮችን ይመለከቱ የነበረበት ጊዜ ነው።

ፍሬምናጦስ ከአክሱም ተሰናብቶ ወደ ግብጽ የሄደበት ጊዜ ወቅቱ የአርዮስን ስህተት ለመቃወም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኒቅያ ጉባዔ የተቀመጡበት ጊዜ ነበር። የአርዮሳዊ የስህተት ትምህርት መሥራች የሆነው አርዮስ የተወለደው በመጀመሪያዎቹ ዘመናት የክርስትና ሃይማኖት ማዕከል ተብላ ትጠራ በነበረው በሊቢያ (ሰሜን አፍሪቃ) ውስጥ ነው። " ክርስቶስ የአምላክነት ባህርይ ሊኖረው አይችልም " የሚል መከራከሪያ በማንሣቱ በየካቲት ወር 325 ዓ.ም በኒቅያ የተሰበሰበው የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከፍተኛ ጉባኤ ያወገዘው የቤተ ክርስቲያን መሪ የነበረ ሰው ነው። ይህን በመሰለ ወቅት ወንጌል ወደ ኢትዮጵያ ቢገባም ቀደም ብሎ በተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ከ100 ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ጉባኤዎች በተከታታይ ሲደረጉ ቆይተዋል። ከፍተኛ መከፋፈልና መለያየቶችም ተፈጽመዋል።

በጥቅምት ወር 451 ዓ.ም በኬልቄዶን ከተደረገው 4ኛው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከፍተኛ ጉባዔ በኋላ " የኬልቄዶን ጉባኤ የተጠናቀቀው ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ የሚለውን የሁለት ባህርይ አቋም በማጽደቅ ነው። "የግብጿ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ግን የተዋሕዶን ትምህርት ያዘች። የኢትዮጵያዋም ቤተ ክርስቲያን ግንኙነቷ ከዚህች ቤተ ክርስቲያን ጋር በመሆኑና ራሷን ችላ ገና ያልቆመች በመሆኗ ይህችን ቤተ ክርስቲያን ከመከተልና የአንድ ባህርይን ትምህርት ከመቀበል ሌላ አማራጭ አልነበራትም። በትምህርት ብቻ ሳይሆን በማናቸውም ግንኙነቶች ጥብቅ ቁርኝቷ ከእስክንድርያ ጋር ሆነ።

በ500ዎቹ ዓመታት ውስጥ "የአንድ ባህርይ" ትምህርት (monophysitism) አባ ያዕቆብ በተባለ የሶሪያ ቤተ ክርስቲያን መሪ ተጠናክሮ ተቀረጸ። ያዕቆባውያን የተሰኙት ተከታዮቹም መበራከት የጀመሩት ከዚያን ጊዜ በኋላ ነበር ። የግብጽ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን

የሃይማኖት ጽሑፎችና የሥነ መለኮት ትምህርቶችም በዚህ ጊዜ በብዛት ተጽፈው ተዘጋጁ። " በረኽኝነት " የተባለው የብሕትውና ልምምድ በስፋት መጀመርም የዚህ ጊዜ ክስተት ነበር፤ "በረኽኝነት ዓለምን ለመሸሽ ወደ ገዳም ወይንም ወደ በረሃ በመሄድ የመቀመጥ ስሜት ነው።"[15] ይህን መሰሉ ልምምድ በጥቂቱ ቀደም ብሎ የነበረ ቢሆንም (የቀድሞው ከስደትና ዓለማዊነትን ከመሸሽ-የተነሳ ሲሆን) የበረኽኝነት ሽሽት ግን ከራሷ በዘመኑ ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጭምር ነበር። ምክንያቱም የዘመኑ ቤተ ክርስቲያን ከአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን መልኳም ሆነ ይዘቷ እየተለወጠ በመምጣቱ ጭምር ነው። በዚሁ በ6ኛው ምዕተ ዓመት የግብጿ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን በውስጧ ብዙ መከፋፈል እንደነበረባት አንድ የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምሁር እንዲህ ጽፈዋል፤

> ወደ 6ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ገደማ ብቻ በግብጽ ሃያ የአንድ ባህርይ (Monophysite) ቅርንጫፍ ስህተቶች (Sects) እንደነበሩ ይነገራል። ከነዚህ መካከል አንዱ ስሉስ አምላክነት (Tri-theism) የሚባለው በሥላሴ ሦስት አማልክትነት (እግዚአብሔሮች) እንዳሉና እያንዳንዳቸውም ከሌላው በባህርይ የተለያዩ ናቸው የሚል እምነት ነበረው።[16]

ከክርስትና ያፈነገጠ ጉልህ ስህተትም ይፈጸም ነበር። በዚሁ ጊዜ የጊዜው ታዋቂ ዓለምም በፖለቲካው ረገድ ከሁለት ጎራ በመከፈሉ የምዕራቡ የሮም፥ የምሥራቁ የቢዛንቲን መንግሥት ተባሉ። የቢዛንቲን ንጉሥ ዮስቲንያን የግብጿ የኮፕቶች ቤተ ክርስቲያን መለየቷን አልወደደምና አንዲት እውነተኛ እና ቀጥተኛ (ኦርቶዶክስ) ቤተ ክርስቲያን ብቻ በግዛቱ እንድትኖር በመውደዱ የግብጿን ቤተ ክርስቲያን ማሳደድ ጀመረ። ኦርቶዶክስ የሚለው ቃል የያዘው ፅንሰ ሃሣብ ቀጥተኛ የሚል ትርጉም ነው። ይህ ስደት እስከሚቀጥለው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ቀጠለ። በአሳዛኝ ሁኔታ የሚቀጥለው ክፍለ ዘመን ግን ግብጽ በእስልምና መዳፍ ስር የወደቀችበት ጊዜ ሆነ።

በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ የኢትዮጵያዋ ቤተ ክርስቲያን የግብፅ ኦርቶዶክስን ፈለግ የምትከተል ስለነበረች ቀጥተኛ ተሳታፊነት የሌላት "ተቀባይ" ቤተ ክርስቲያን በመሆን በተቀደደላት ፈር ቀጠለች።

ስርዓቶችዋ፥ ሥነ መለኮታዊና አስተምህሮታዊ ይዘቶችዋም የአስከንድርያ ቅጅ በመሆን ቀጠለ። ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ በነበሩት አንድ ክፍለ ዘመን ተኩል ያህል ጊዜያት ውስጥ ክርስትናና ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ የተደረጉ ዝርዝር ነገሮች አይገኙም፡፡ ጎላ ያለ ነገር የሚታየው በዐፄ ካሌብ ዘመን ሲሆን በኢዛናና በካሌብ መሐል የአንድ መቶ አምሳ ዓመታት የጊዜ ርቀት አለ። በነዚሁ ጊዜያት ግን በሰሜን አፍሪቃና በሜዲቴራኒያው የክርስቲያን ዓለም የአስተምህሮት ክርክሮች እየተጧጧፉ አንዱ አንዱ ቡድን፥ ሌላ ጊዜ ሌላው ሲረታ፥ አንዱ ንጉሥ አንዱን ቡድን፥ ሌላው ደግሞ ሌላውን ሲደግፍ፤ ረቺው ቡድን፥ ሲደላው ተረቺው ሲታሰርና ሲሰደድ ቆይተዋል። ለምሳሌ በ423 ዓ.ም. ንስጥሮስ ሁለት ባህርይ ብሎ በማስተማሩ እርሱ ተጋዘ፥ ተከታዮቹም ወደ ምሥራቅ ተሰደዱ። በ441 ዓ.ም. ደግሞ የአንድ ባህርይ ደጋፊ የሆነው አባ ዲዮስቆሮስ የቁስጥንጥንያውን አባ ፍላብያናስን ተከራክሮ ስለረታ የፍላብያናስ ወገኖች ተሰደዱ። በ443 ዓ.ም. ደግሞ ዲዮስቆሮስ ተረቺ ሆኖ ሲታሰር ተከታዮቹም ተሰደዱ። እነዚህ ስደተኞችም የአንድ ባህርይ ደጋፊዎች ወደ ሚገኙባቸው አገሮች ሄደዋል። በእነዚህ ዓመታት ሁሉ ግን የአክሱም መንግሥት ቤተ ክርስቲያን የአንድ ባህርይ ደጋፊ ጳጳስ ሲላክላት ቆይታለች።

በዚህ ጊዜ ነው ስደተኞችና የሃይማኖታቸው መልእክተኞችም (ሚስዮናውያን) ሆነው ዘጠኙ ቅዱሳን (ዘጠኙ መነኮሳት) የተባሉት የመጡት። የጊዜውን የግዕዝ ቋንቋና ጥንታዊውን የሳባ ፊደል እንዲሁም የሕዝቡን ባህል በማጥናት በተለያዩ አቅጣጫዎች በመሰማራት በአክሱምና አካባቢዋ ቆይቶ የነበረውን እምነት አሰራጭተዋል። ለሳባዊ ፊደሎች አናባቢ ምልክቶችን ጨምረው ፊደሉን አሁን በምንጠቀምበት መልክ በማዘጋጀት መጽሐፍ ቅዱስንና ሌሎችንም ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተርጉመዋል። ከሥነ ጽሑፍ ጋር የሥነ ጥበብ ዕድገት እንደነበረም ይወሳል።

ከጅማሬው አንስቶ የኢትዮጵያ ክርስትና ከቤተ መንግሥት እና ከነገሥታት ጋር የተያያዘ ነበር፡፡ ከነዚህም ዘጠኙ ቅዱሳን ጥቂቶቹ ከነገሥታቱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው፥ ሃይማኖቱም መንግሥታዊ ሃይማኖት ነበር ለማለት የሚያስችሉ በቂ ማረጋገጫዎች ይገኛሉ። እነዚህ ሰዎች ያስፋፉት ሌላው ነገር ገዳማዊ ኑሮን ነው። ከተራ ሰዎች ጀምሮ እስከ

ንጉሥ ድረስ (ለምሳሌ ካሌብ) ወደ ገዳም ገብተው ኖረው ሞተዋል። (ይህ ገዳማዊ ንቅናቄ ከእነዚህ ቀደም ብሎ በግብጽም የተለመደ ባህል ሆኖ ሰዎቹም "በረኸኞች" ይባሉ እንደ ነበር ተመልክቷል። ቀጥሎ ባሉት ክፍለ ዘመናት እስልምና የአፍሪቃን ሰሜን ወርሮ በቁጥጥሩ ሥር በሚያውልበት ጊዜ በግብጽ የአንድ እና ሁለት ባህርይ ክርክር አገርሽቶ ነበር።ከጠባቸውና አቋማቸው መብሰል የተነሳ የእስክንድሪያ ክርስቲያኖች የቁስጥንጥንያዎቹን የሁለት ባህርይ ደጋፊ ባለሥልጣናት ከግብፅ ለማስወጣት ሲሉ ከእስላሞች ጋር ተባበሩ ይባላል።[17]

እስልምና ወደ ኢትዮጵያ መጀመሪያ የገባው በሰላማዊ መንገድ ስለነበር ችግር አልተፈጠረም፤ በኋላ ግን የባህር በሮችን በሙሉ ተቆጣጥሮ ስለዘጋና የመካከለኛው ምሥራቅና የሰሜን አፍሪቃ አብያተ ክርስቲያናትም እየተዳከሙና እየከሰሙ ሲመጡ ከነሱ ጋር የነበረው ግንኙነት ቀርቶ የተጀመረው ዘይቤ በሃይማኖት ሽፋንነት የወቅቱን መንግሥታት በጎ ፈቃድ የመሻት አዝማሚያ ብቻ መስፋፋት ያዘ። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሰሜን ፈላሻዎችና የአገው ዛጉዬዎች በየተራ እየተነሱ ቀድሞም ያልደመቀውን ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ እኔ እሻል እኔ እገዛ በሚል ሽኩቻ በአንድ በኩል ሲያዳክሙ በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ጊዜ ከአውሮጳ ወደ ቅድስት አገር ኢየሩሳሌም የተነጣጠረው የመስቀል ጦርነት ሃይማኖትን ከፖለቲካው ጋር ፈጽሞ አዋሃደው። "ቅድስት አገር ኢየሩሳሌምን ከኢአማንያን መዳፍ ነፃ ለማውጣት"በሚል ቅንዓት በርካታ የመስቀል ጦርነቶች ከ1096-1291 ዓ.ም ባሉት ሁለት መቶ ዓመታት ውስጥ ተፈጽመዋል። በ13ኛው መቶ አጋማሽ ገደማ ኢየሩሳሌም ለትንሽ ጊዜ ነፃ ሆና ያዕቆባውያንና ካቶሊኮች እዚያ አብረው ይሰሩ በነበሩበት ወቅት አንድ ያዕቆባዊ መነኩሴና ጥቂት ዶሚኒካን የሆኑ የካቶሊካውያን ሚስዮናውያንም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ነበር።

እንዲህ እያለ የፖለቲካ ስሜት ያላቸው ካህናትና ጳጳሳት እንዲሁም መንፈሳዊ የሆኑ ነገሥታትም እየተነሱና የየራሳቸውን ሚና ለይተው እየተከራከሩና እየተዋጉ 15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደርሶ ከወንጌል ጋር የተያያዙ ሁለት ተቃራኒ ክስተቶች ተፈጠሩ፡ ፡እኒህም የደቂቀ እስጢፋኖስ የወንጌላዊ እምነት እንቅስቃሴና ይህን እንቅስቃሴ በእንጭጭነቱ ለመቅጨት ንጉሡ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ እና ቤተ ክህነት የወሰዱት የዐጸፋ እርምጃ ነው። ይህ የወንጌል እንቅስቃሴ ከዚያ በፊት ባልታየ መጠን

5. ስብከተ ወንጌል ኦርቶዶክሳዊ ተሞክሮ



የቅዱሳት መጻሕፍት ቅጂ በግዕዝ ቋንቋ

ምንጭ ፡ The Ethiopians.

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወደ ወንጌል አገልግሎት እንድትገባ መልካም ሁኔታዎች የተመቻቹበት ጊዜ ነበር።

5. ስብከተ ወንጌል አርቶዶክሳዊ ተሞክሮ



የቅዱሳት መጻሕፍት ቅጂ በግዕዝ ቋንቋ
ምንጭ ፡ The Ethiopians.

የተዋሕዶ ክርስትና በኢትዮጵያ ገና ከመጀመሪያው አንስቶ የመንግሥት ሃይማኖት ሆኖ መቀጠሉን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተደጋግሞ ተወስቷል። በዚች ምድር ላይ በቆጠረው ረዥም ዕድሜም ከኢትዮጵያ መንግሥት ግዛትና ኃይል መስፋፋት ጋር በተጓዳኝ ሲሰፋ÷የመንግሥቱ አቋም ርዶ እግሮቹ ወደ ማእከላዊውና የሰሜን ኢትዮጵያ ክልሎች ሲያፈገፍግ አብሮ እየተሰበሰበ አሳለፈ።[18]

የማእከላዊው መንግሥት አቅም ተዳክሞ በሥሩ የነበሩትን ዳር አገሮች ሲለቅ በጀግ አምኖ የነበረው ነዋሪው ሕዝብ ወደ ቀደመው ልማዱ መመለሱ ወይንም እንዲመለስ መገደዱ አልቀረም።

በዚያው ልክ ማእከላዊው መንግሥት ኃይሉን አጠራቅሞ ለዘመናት አሻፈረኝ ብለው ሳይገብሩ የኖሩትንም ሆነ በጦር ኃይል አዲስ በሚያቀናቸው አገሮች ውስጥ የሠራዊቱን ፍለጋ ተከትሎ ቤተ ክርስቲያን መመስረት የቆየ ልማድ ነበር።[19]

አልፎ አልፎ ግን ከቀጥተኛ መንግሥታዊ ተጽእኖ የጸዱ አርቶዶክሳዊ የስብከተ ወንጌል አገልግሎቶች መከናወናቸውና አገርኛ የሆኑ ሐዋርያዊ ድርጅቶች ተነሥተው ታላላቅ የወንጌል ሥራዎችን ማከናወናቸውን የታሪክ ምሑራን አውስተዋል።

መሠረት ስብሐት ለአብ በርካታ ድርሳኖችን በመጠቃቀስ የጥቂቶቹን ሐዋርያዊ ድርጅቶች ስም ለታሪክ ማስታወሻ ከመዘገቧቸው መካከል፤


- ማኅበረ ዶጌ (ማኅበረ ጻድቃን ዘ ዶጌ) በአክሱም
- ማኅበረ በኩር - በእንደርታ፥
- ማኅበረ ጻድቃን ፥በወራጉት - በአጋሜ ዋና ዋናዎቹ ነበሩ።

እኒህ ከላይ የጠቀስናቸው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምሑር እንደሚሉት "ከሁሉም ጎላ ብሎ የሚታየውና እስከ ዘመናችን ያንጸባረቀው ሐዋርያዊ ድርጅት ግን ከመጨረሻዎቹ ነገሥታት በአንዱ ይኸውም ከ837- 856 በነገሠው በንጉሥ ድግና ይዥን ዘመነ መንግሥት መቶ አምሳ ባለወንበር መምህራን የእንበረም ተወላጅ በሆኑት በአባ ይድላ መሪነት ለስብከተ ወንጌል ወደ ሸዋ ምድር መላካቸው ነው"[20] በውጤቱም በቡልጋ አካባቢ የወንጌል ብርሃን ተቀጣጥሎ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሊቋቋሙ ችለው ነበር።

ከዚህ ሌላ በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ "ሐዲስ ሐዋርያ " በመባል የሚታወቁት አባ ተክለሃይማኖት ከሞላ ጎደል የዘመናዊቷን ደቡብ ኢትዮጵያ እየተዘዋወሩ በአደረጉት ስብከተ ወንጌል ብዙ ሕዝብ ክርስትናን ከመቀበሉም በተጨማሪ ጥቂት ቤተ ክርስቲያናትም ለመትከል በቅተው ነበር። ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ይህንን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት አገልግሎት በተመለከተ፤ " በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን


የተደራጀ ሐዋርያዊ ተልእኮ ታሪክ ዋነኛ ተጠቃሽ ነው " [21] በማለት ገልጸውታል።

በ1215 ዓ.ም በቡልጋ አውራጃ ምድረ ጽላልሽ በተባለ አካባቢ የተወለዱት አባ ተክለ ሃይማኖት "በደቡብ ኢትዮጵያ ከፈጠጋር (አዳማ) እስከ ቤዛም (ወለጋ) ከማልበርዲ እስከ ወላሞ ድረስ " [22] እየዞሩ ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት እንደ ሞከሩ ይነገርላቸዋል።



የቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ከ13 – 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

ምንጭ ፡ Church and State in Ethiopia



የቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ከ13 – 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

በጊዜውም ከምዕራብ ሸዋና ከደቡብ ጎጃም አንስቶ የዛሬዋን የደቡብና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን አያሌ ክፍሎች ሲገዛ የነበረውን ንጉሥ ሞተሎሚን አሳምነው እንዳጠመቁት ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ልማዳዊ ታሪክ ይዘከራል። በርካታ የታሪክ ጸሐፊዎችም ከብዙ ጥንቃቄ ጋር እውነትነቱን ይጋራሉ።[23]

በተለያዩ የታሪክ ጸሐፊዎች የዳሞት ንጉሥ፥ የሃዲያ ንጉሥ አንዳንዴም የወላሞና የሃዲያ ንጉሥ በመባል የሚታወቀው ሞተለሚ የአባ ተክለ ሃይማኖትን ስብከተ ወንጌል የተቀበለው በቀላሉ አልነበረም፤ እንዲያውም ሊገድላቸው ፈልጎ ነበር ይባላል። ነገር ግን በፊቱ ባደረጉት ተአምራት ተማርኮ ክርስትናን እንደ ተቀበለና በአገሩ በዳሞት እንደ ተጠመቀ በዝዋይ ሐይቅ ውስጥ ባለች ደሴት የተገኙ ገድሎች አረጋግጠዋል። ይህንኑ ታሪክ አስመልክቶ ጸሐፌ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ እንደሚከተለው ተርከዋል።

> ...ኋላም በሳቸው (በአቡነ ተክለሃይማኖት) ያደረ መንፈስ ቅዱስ እየረዳቸው ከዚያ ዳሞት ከሚባለው አገር ሄደው ያገሩንም ገዢ ሞተለሚን አሳምነው እጥምቀው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተሠርቶ ነበር። ኋላ ግን ግራኝ ተነሥቶ አጥፍቶት ሃይማኖት የጠፋበት አገር ሆነ። ይህም ታሪክ በገድለ ሃይማኖት ይገኛል።[24]

እኒሁ ታሪክ ጸሐፊ ዳግማዊ ምኒልክ በ1887 ዓ.ም ወደ ወላይታ ለመዝመት የተነሣሡበት ምክንያት " ሞተሎሚ የተጠመቀበት አገር ሃይማኖት ጠፍቶበት መኖሩ እያሳዘነም ለማቅናት ጊዜ ሲፈልጉለት ነበር።...ጊዜው ሲደርስ...ዘመቻ ጉዞ ሆነ "[25] በማለት ዘግበዋል።የተነሣንበት ጉዳይ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ዐውደ ትምህርትን ያገናዘበ ስብከተ ወንጌል ለደቡብ ኢትዮጵያ ነዋሪ ሕዝብ ለማዳረስ ቢያንስ ከ400 ዓመታት በፊት የተደረገውን ሙከራ ለማሳየት እንደሆነ ልብ ይሏል።

ወደ አባ ተክለሃይማኖት ስብከተ ወንጌል ተሞክሮ ስንመለስ የደብረ ሊባኖስን ገዳም ከመሠረቱ በኋላ የኖሩት ለሃያ ዘጠኝ ዓመት ነው።[26]

በዚያን ወቅት ከሩቅም ከቅርብም ዝናቸውን እየሰሙ መጥተው የብሕትውና ይዘት ያለው መንፈሳዊ ትምህርት የቀሰሙ በርካታ ናቸው። ከዚህም የተነሣ እሳቸው በ1313 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ የጀመሩትን አገልግሎት ለማስቀጠል ፊልጶስና አናሪዎስ የተባሉት የእርሳቸው ደቀመዛሙርት ከዝቋላ ተራራና ከዝዋይ ደሴት በመነሣት አባው ያልደረሱባቸውን አውራጃዎች ሁሉ ለመድረስ በቅተዋል። እንዲያውም ፊልጶስ የደብረ ሊባኖስ እጨጌ ከሆኑ በኋላ የሐዋርያትን ምሳሌ በመከተል ሌሎች አሥራ አንድ ደቀ መዛሙርት መርጠው አሥራ ሁለተኛ ራሳቸው ሆነው በብዙ አውራጃዎች የተዋሕዶን ዐውድ ያልለቀቀ ስብከተ ወንጌል እንዳካሄዱ ታውቋል።

ይህም በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ደማቅ ሥፍራ ሊያሰጣቸው ችሏል።

በዚች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንዲህ አይነቱ መነቃቃትና የወንጌል ሥራ ሳያቋርጥ በሙላት ተካሂዶና ሥነ መለኮታዊው ይዘት በሚገባ ተቀርጾ የምሥራቹን ቃል በማዳረስና በክርስቲያናዊ የሕይወት መታደስ ላይ ቢያተኩር ኖሮ በነፍስም በሥጋም አገራችንና ሕዝባችን ከአሁኑ በተሻለ አቋም ላይ በደረሱ ነበር።

6. ተቀጣጥሎ የከሰመ ወንጌላዊ መነቃቃት

የታሪክ ሊቃውንት ከሮም ውድቀት በኋላና በመካከለኛው ዘመን እስከ ተሐድሶው ጊዜ የነበረውን ዘመን "የጨለማው ዘመን" ብለው ይጠሩታል። የጨለማው ዘመን የሚለው ስያሜ የተሠጠው በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሳይሆን ከመሠልጠንና ካለመሠልጠን ጋር በተያያዘ ሁኔታ የአውሮጳ አቅኚዎች የተጠቀሙበት ገለፃ ነው። ይህ የሆነው በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ወደ ፖለቲካ በመግባቷ፥ ከዚያም በአረማውያንና በኋላም በእስልምና በመወረሯ ምክንያት የቀድሞው የግሪክና የሮም ሥልጣኔ እየደበዘዘ በመሄዱ ነበር። ይሁን እንጂ እውነተኛው መንፈሣዊ ሕይወት ጨርሶ ተዳፍኖ አያውቅም። በየዘመናቱ የክርስቶስን ሕይወት ያንጸባረቁና የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን አይነት ጎብረት ሊመሠረቱ ሞክረው የተሳካላቸውም ያልተሳካላቸውም ብዙዎች ነበሩ።

ከዓለም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ወደ አገራችን መለስ ስንልም ልማዳዊ ከሆነው አካሄድ ወንጌላዊ ወደሆነው እምነት የተራመደ የጎላ እንቅስቃሴ የተከሰተበት ጊዜ ነበር። ይህ የሆነው ከአውሮጳው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አንድ ምዕተ ዓመት ያህል ቀደም ብሎ ነው። እንቅስቃሴው የተወለደው ጥቂት ቀደም ብሎ ቢሆንም ጎልቶ የታየው ግን በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት (1434 -68) ነው። ይህ እንቅስቃሴ "ደቂቀ እስጢፋኖስ" ተሰኝቶ በጀማሪው እስጢፋኖስ ስም ተከታዮቹ ያወጡት መጠሪያ ነው። በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስለ እነዚህ ሰዎች እንዲህ ተጽፏል፤

> ከዚህም ሌላ በዘመናቸው (በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ማለት ነው) ዜና መዋዕላቸው እንደሚለው ደቂቀ እስጢፋኖስ የሚባሉ ለእመቤታችንና ለቅዱስ መስቀል ስግደት አይገባም የሚሉ መናፍቃን እንደተነሱ ይጽፋል። ይኸው ዜና መዋዕል እንደሚለው እነዚህን መናፍቃን ንጉሡ ባሉበት ሊቃውንቱ ተከራክረው ረቷቸው። ከዚህ በኋላ እነ ደቂቀ እስጢፋኖስ ለፍርድ ቀረቡ። ንጉሡም ፍርዳቸውን ከምዕመናን እንዲቀበሉ የተሰበሰቡትን

ምዕመናን ጠየቁ። ሁሉም በሞት ቅጣት እንዲቀጡ በየነባቸው። በመጨረሻም አፍንጫቸውን ተፎንነው (ተቆርጠው) ምላሳቸውን ተቆርጠው በደንጊያ ተወግረው የካቲት ሁለት ቀን ሞቱ፤ በ38ኛው ቀን በዚያ ቦታ ብርሃን ወርዶ ታየ። ስለዚህም ይህችን ቦታ ደብረ ብርሃን ብለው ሰየሟት።"[27]

የእስጢፋኖስ ተከታዮች የሆኑት በጻፉት ታሪክ ደግሞ ብርሃን ወርዶ መታየቱ ሳይሆን በዕለቱ መብረቅ ወርዶ ታላቅ እሳት ቤተ መንግሥቱን ማያያዙና ማውደሙ ነው የተነገረው።

እስጢፋኖስ በተወለደ ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሥ ቀዳማዊ ዐፄ ዳዊት ነበሩ። በዚሁ በዐፄ ዳዊት ዘመነ ንግሥ ነበር ግማደ መስቀል እና ሌሎችም ስዕሎች ከኢየሩሳሌም መጥቷል የሚባለው። ከዐፄ ዳዊት በኋላ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ እስኪነግሡ ድረስ ከጥቂት ወራት እስከ ጥቂት ዓመታት ያህል እየነገሡ ስድስት ነገሥታት በየተራ ዙፋን ላይ ተቀምጠዋል። ከነዚህም አራቱ የዐፄ ዳዊት ልጆችኅ ወንድሞቻቸው ነበሩ። እነዚህ ሁሉ ተራ በተራ ሲነግሡ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ " መንኩሰው " ገዳም ይኖሩ ነበር። መንግሥት ከወንድም ወደ ወንድም ልጅ ሲተላለፍ በማየታቸው ግን ከገዳም ወጥተውና ቆባቸውን ጥለው ሁለት ሚስቶች አግብተው ሊነግሡ ችለዋል።

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በአስተዳደርና በግንኙነት ረገድ ስማቸው የተጠራ ንጉሥ ናቸው። ለሃይማኖት ፍጹም ቀናተኛ በመሆናቸው ሰዎች ከተለያዩ አምልኮ ስርዓቶች በቅጣትና በአዋጅ እንዲመለሱ አድርገዋል። አዋጁም በግንባራቸው 'በአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ' የሚል፥ በቀኝ እጃቸው 'በክርስቶስ አምላክ ዲያብሎስን ክጃለሁ' የሚል እና በግራ እጃቸው ደግሞ 'የተረገመውን ደስክን ክጃለሁ እኔ ለዓለም ፈጣሪ እናት ለማርያም አገልጋይዋ ነኝ' የሚል እንዲጻፍ ተደርጓል። ይህን ያልፈጸመ በስጋው እንዲቀጣ ትዕዛዝ ወጣ። የቤተ ክህነት ሰዎችም የዚህ ተባባሪ ነበሩ።ደስክ በዚያን ወቅት የነበረ የባዕድ አምልኮና የእርኩሳን መናፍስት አሰራር ነበር::

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ንጉሥ ብቻ ሳይሆኑ በገዳም የኖሩ ጸሐፊም ነበሩና ራሳቸው እየጻፉና ሌሎቹን እያጻፉ በዘመነ መንግሥታቸው ለማርያም ለመስቀልና ለስዕል መስገድ እንደሚገባ የሚናገሩ በርካታ መጻሕፍት እንዲበዙ አድርገዋል። ተዓቅቦ ምስጢር፥ መጽሐፈ ብርሃን፥ ተአምረ ማርያም፥ ርቱዓ ሃይማኖት፥ ጦማረ ትስብእት፥ መጽሐፈ ምዕላድ፥ አርጋኖን ድንግል፥ ዘለፋ እስጢፋ... ሌሎቹም የተፃፉትና ተተርጉመው የተሰናዱት በዚህ ጊዜ ነው።

ወደ እስጢፋኖስ ታሪክ ስንመለስ፥ እስጢፋኖስ የሚለው መጠሪያው የትውልድ ሳይሆን የምንኩስና ስሙ ነው። የተወለደውም በ1380 በትግራይ ክፍለ ሐገር በአጋሜ አውራጃ ከመኳንንት ቤተሰብ ነው። ወደ ቆየጻ ገዳም የገባው ለመጽደቅና ለነፍሱ ደኅንነት ለማግኘት በመሆኑ በጾም በጸሎት በስግደትና በአድካሚ ሥራዎች ራሱን በጣም ጎዳ። ቢሆንም ከቃለ እግዚአብሔር አንድ እውነት ተረዳ፤ ያም ደኅንነቱን ማረጋገጥ መቻሉን ነበር። መጻሕፍትን በመመርመርና እየጻፈ በመሸጥም በእጁ ሥራ የገዳም ኑሮውን ይገፋ ጀመር። ይህን የተረዳውንም እውነት ለሌሎች የማስተላለፍ ሸክም አደረበትና ትምህርቱን በጽሑፍ አሰናድቶ ከጻፋቸው የማስተማር ፈቃድ አግኝቶ ማስተማር ጀመረ። ተከታዮቹም በቁጥር እየበዙ፥ በመንፈሣዊ ዕውቀታቸው እየበሰሉ፥ የእጅ ሙያም በመውደዳቸው ከሌላው የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን የተለዩ በመሆናቸው የቅንዓት ዒላማ ሆኑ፥ ለስደትም ተዳረጉ፤ እስጢፋኖስም ሦስት ዓመታት ታሠረ። ከተፈታም በኋላ መለስተኛ ነፃነት አግኝቶ የአማኞች ማህበሮችን አቋቁመና በሥርዓት እንዲኖሩና ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያጠኑ አበረታታ።

ጥቂት ቆይቶም ጠንካራና የተቀነባበረ ክስ በመነኮሳቱ አማካይነት በንጉሡ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፊት ተመሠረተበት። እስጢፋኖስ ወደ ንጉሡ ሲቀርብ ለንጉሡ ካለመስገዱም ባሻገር ንጉሡን በመገሰጹና ቤተ ክርስቲያንና መንግስት ለየብቻ እንዲሆኑ አበክሮ በመናገሩ ንጉሡ ደግሞ እኔ የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ነኝ በማለቱ በብርቱ ተደበደበና ታሠረ። ከዚህ ሁሉ ስቃይ በኋላ ተለቅቆ ሊሄድ ሲዘጋጅ እንደገና ለንጉሥ ለማርያምና ለመስቀል እንደማይሰግድ ስለተደረሰበት በድጋሚ ተከሰሰ።በዚህ ጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል እየጠቀሰ እንዲሟገት ጠይቆ ዕድል ሳይሰጠው በአክሱም ስርዓተ ንግሳቸውን ሊያካሂዱ በሄዱት በንጉሡ ትዕዛዝ ወደ ሸዋ (ይፋት) እንዲመጣ

ተደረገ። የንጉሡም ወታደሮች የእጆቹን ቆዳ ገፍፈው አሰቃይተው በእስር ቤት ጣሉት። እስጢፋኖስም የክርስቶስን ስም ደጋግሞ በመጥራት በዚህ እስር ቤት ውስጥ ሕይወቱ ልታልፍ በቅታለች።



በዐፄ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (1434 – 1468)
የተሳለ የቅድስት ማርያም ሥዕል
ምንጭ ፡ Church and State in Ethiopia

እስጢፋኖስ ቢሞትም ማኅበሮቹ ግን ጠነከሩ። ንጉሡም እነዚህን ማኅበሮች (ቤተ እስጢፋ) ለመቅጣት በቁጣ ተነሳስቶ ብዙዎችን ገደለ። አማኞቹ ግን ለመከራም ለሞትም የቆረጡ ሆኑ። 'መናፍቃን' እየተሰኙ ትልቅ መንገላታት እና ዕልቂት ፈንታቸው ሆነ። በቤተ ክርስቲያን ትይዩ መስቀል ይተከልና ሰው ሁሉ ለዚያ እንዲሰግድ አዋጅ ታወጀ። የእስጢፋኖስ ተከታዮች እንደማይሰግዱ ስለሚታወቅም የተደበቁ ቃሬሮች እያደፈጡ ይይዟቸውና ለፍርድ ያቀርቧቸው ነበር። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ብዙዎች ስለ እምነታቸው መስዋዕት ሆኑ። ሞታቸው የስቃይ እንዲሆን ደግሞ አፍንጫና ምላሳቸው ይቆረጥ ነበር። በመጨረሻም ንጉሡ እነዚህን ብቻ የሚመለከት አዋጅ አወጣ። የአዋጁ ሙሉ ቃል ትርጉም እንዲህ የሚል ነው፤

> በሁለቱም ጊዜያት ድንግል የምትሆን የግርያም ምዕመናን የሆናችሁ ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ! እንዲህ እላችኋለሁ፤ ማናቸውም ሰው ሁሉ ደቂቀ እስጢፋን የተቀበለ ከእነርሱ ጋር የተባበረ በቤቱ ውስጥም ያኖራቸው ወይም በቤተ ክርስቲያኑና በርስቱ ምድር ያኖራቸው ቢገኝ፥ ሹመት ያለው ቢሆን ከሹመቱ ይሻር፥ ቤቱም ይዘረፍ፥ ገንዘቡ ሁሉና ያለውም የምድሩ ርስት ለባዕድ ይሁን። ሊቃነ ካህናት ንቡራነ ዕድ የቤተ ክርስቲያን ሹማምንትና መነኮሳትም ሁሉ ሕዝቡም ሁሉ እነርሱን ሲደብቋቸው ከተገኙ በእነርሱ ላይ ከፍ ያለ ቅጣት ይፈጸምባቸዋል። ሹመታቸውና የምድር ርስታቸው ለሌላ ይሁን። ከእነርሱ ጋር ተባብረዋልና ነው። እነዚህ ደቀ እስጢፋ ግን ለድንግል ማርያምና ለአንድ ልጅዋ መስቀል መስገድን እምቢ ያሉ ናቸውና፥ በእውነት አይሁድ ናቸው። የእነርሱ ቅጣት ግን ሞት መሆን አለበት። ያገኛቸውም ሁሉ በጽኑ መከራ ይቅጣቸው። ቃላቸውን ሰምተን በአደባባያችን ሽንጎ እንድንፈርድባቸው ወደ አደባባያችን ያምጣቸው እንጂ መግደልን ግን እርሱ ራሱ አይግደላቸው። እንደዚሁም ከደቀ እስጢፋ የሆነውን ሰው አግኝቶ ሰላምታ የሰጠው ሰው ሁሉ ዕድል ፈንታው ደቀ እስጢፋን ለተቀበሉ እንደሚደረግባቸው ይሆናል።"[28]

ከዚህ አዋጅ በኋላ ጽኑ ስቃይ በደቂቀ እስጢፋኖስ ላይ ወደቀ። ይህ ጽኑ ስቃይ ራሳቸው ደቀ እስጢፋ በጻፉት በገድለ አጎው እና አሳዳጆቻቸው በጻፉት በተአምረ ማርያም ላይ በጉልህ ተጽፎ ይገኛል። እነዚህ አማኞች ስደቱ ሲያይልባቸው ወደ በረሃ ወደ ጫካና ወደ ዋሻ ገቡ። ቆይቶም በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ልጅ በዐፄ በዕደ ማርያም ዘመነ መንግሥት ተከራክረው ፍትህ

እንደሚያገኙ ተነግሯቸውና ተዘጋጅተው ቢቀርቡም ንጉሡ አሳባቸውን በመቀየር አባታቸው የፃፈውን ዘለፋ እስጢፋ የተሰኘ መጽሐፍ አምጥተው በማንበብ የባሰ ፍርድ ፈረደባቸው። ለክርክር የቀረቡት በአንበሳ እንዲበሉ ሲደረግ በጫካ በበረሃና በዋሻ ያሉት ገሚሶቹ በረሃብና በጥም፥ ገሚሶቹ ደግሞ በእስላም ወራሪዎች ሲገደሉ፥ከቀሩት ብዙዎቹን ንጉሡ ዐፄ በዕደ ማርያም ፍለጋቸውን እየተከተሉ የሚገድሏቸውን ሠራዊት አሰማርቶ ጨርሶ ባያጠፋቸውም እንቅስቃሴያቸውን ግን ገታው። እንግዲህ እስጢፋኖስ ከሞተ ከ100 ዓመታት በኋላ ነበር የምዕራብ አውሮጳው ተሐድሶ የተጀመረውና ቆይቶም ወንጌላዊ እምነት ወደ አገራችን እንደገና የገባው።

የግርጌ ማስታወሻዎች
ምዕራፍ አንድ

[1] መሠረት ስብሐት ለአብ ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአስተዋፅኦ ፤ ገጽ 9።

[2] ገብረ ሥላሴ (ጸሓፌ ትእዛዝ)፣ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፤ ገጽ 17 – 19 ።

[3] Tenny, Merrill. New Testament Survey p.10

[4] ማኅበረ ቅዱሳን ፣ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ ፤ ገጽ 93–95 እና ገጽ 145–146 ።

[5] ለዚህ የታሪክ መጽሐፍ ረቂቅ ግምገማ የቀረበ አስተያየት ፣ መጋቢት 17 ቀን 1990 ዓ·ም· ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት ፣ አዲስ አበባ።

[6] ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ ፣ ገጽ 95 ።

[7] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ኑቢያ ፣ አክሱም ፣ ዛጉዬ ፤ ገጽ 142 ።

[8] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል ገጽ 10 ።

[9] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ፣ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት ፤ ገጽ 110።

[10] Ullen Dorf Edward. The Ethiopians P. 122

[11] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት····· ገጽ 122

[12] የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአስተዋፅኦ ፤ ገጽ 9 ።

[13] ዝኒ ከማሁ ፣ ገጽ 23

[14] ዝኒ ከማሁ ፣ ገጽ 9

[15] ገነ ከማሁ ፡ ገጽ 39

[16] Hildeora ıdt, Jonathan. History of The Church in Africa P. 189.

[17] የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል ፡ ገጽ 26 ።

[18] Ta ıdes ıe Tamrat. Church And State in Ethiopia P. 156.

[19] ዝኒ ከማሁ ፡ ገጽ 173 ።

[20] የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በአስተዋፅኦ ፡ ገጽ 55 ።

[21] Church and State In Ethiopian P. 167.

[22] የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአስተዋፅኦ ፡ ገጽ 55 ።

[23] የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ አፄ ልብነ ድንግል ፡ ገጽ 20 ።

[24] ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፡ ገጽ 219 ።

[25] ዝኒ ከማሁ ፡ ገጽ 219

[26] Church And State in Ethiopia P. 172.

[27] የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአስተዋፅኦ ፡ ገጽ 69 70 ።

[28] ዝኒ ከማሁ ፡ ገፅ 71 ።